# የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት(መዐሕድ)
## All Amhara People's Organization (AAPO)

E-mail: aapomeahd@gmail.com
Website: www.aapo-mahd.org

የካቲት 19 2010 ዓ.ም.

ቁጥር: **aapo026/18**

### ከመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት የተሰጠ መግለጫ

የተከበርከው የአማራ ህዝብ

የተከበራችሁ የመዐሕድ አባላትና ደጋፊዎች

እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ

የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት በውህደት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በጊዜያዊ አመራር ተዋቅሮ የስድስት ወራት የሽግግር ጊዜ ማሳለፉ ይታወቃል። ባለፉት ስድስት ወራት መዐሕድ መላው የአማራ ህዝብን በቁርጠኝነት ለማገልገል የሚያስችለውን የአደረጃጀት ባህልና ወቅቱ የሚጠይቀውን ዘመናዊ የድርጅት መዋቅር ሲዘረጋ ቆይቷል። ጊዜያዊ አመራሩም ድርጅቱ የጣለበትን ከፍተኛ ሀላፊነት በብቃት ሲወጣ ቆይቶ የካቲት 3 ቀን 2010 ዓ.ም. በተደረገው የመዐሕድ ጠቅላላ ጉባዔ ለተመረጡ ቋሚ አመራሮች ሃላፊነቱን አስረክቧል። ጠቅላላ ጉባዔው ግልፅ እና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ በማካሄድ የድርጅቱን ሊቀመንበር፣ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበር እና ዋና ጸሐፊን ጨምሮ በድምሩ 15 አባላት ያሉት የዓለም ዓቀፍ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መርጧል፡፡ አዲስ የተመረጡ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትም የተጣለባቸውን ሃላፊነት በብቃት ለመወጣት በጠቅላላ ጉባዔው ፊት ቃል ገብተዋል። የአገርልግሎት ዘመናቸውም ሁለት ዓመታት ይሆናል።

የአማራ ህዝብ አሁንም ቢሆን በተለየ መልኩ በኢትዮጵያ በነገሰው የወያኔ ትግሬ ፋሽስታዊ አገዛዝ የጭቆና ቀንበር ስር እየማቀቀ ይገኛል። አገዛዙ በመቶዎች የሚቆጠሩ የግፍ ታሳሪዎችን ፈታሁ እያለ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩትን ወደ ማጎሪያው እያጋዘ ይገኛል። ግድያ፣ መፈናቀልና እንግልት ከበፊቱ በባሰ መልኩ አሁንም ቀጥሏል። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅም በሁለት ዓመት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ታውጇል። መዐሕድ የአማራ ተወላጆችን በአንድ ጥላ ስር የማሰባሰብ ሂደቱን የቀጠለ ሲሆን ይህን ከግብ ለማድረስ አቅም ላላቸው የአመራር አባላት ሃላፊነትን ሰጥቷል። በመሆኑም የአማራ ህዝብ በአገሩ ኢትዮጵያ ያለምንም ችግር ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመኖር መብቱን ለማረጋገጥና ዘሩን መሰረት አድርጎ የተሰነዘረበትን መጠነ ሰፊ ጥቃት ለመመከት የሚያደርገውን ትግል እንድትቀላቀሉ መዐሕድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ድል ለአማራ ህዝብ!

የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐሕድ)